# የለጋሾች ሚና ለአዳፕቴሽን፤ ለጋሾች መገንዘብ ያለባቸው

ብዙዎች በመልማት ላይ የሚገኙ ሀገሮች የክላይሜት ለውጥ ጫና እንደሚያጋጥማቸው ይገመታል፤ ይህን ለመከላከል ግን በቂ ገንዘብ፣ ዕውቀትና አቅም የላቸውም፡፡ እነዚህ ሀገሮች ለአርዳታ ወደ ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ፊታቸውን ይመልሳሉ፡፡ በነዚህ ሀገሮች የሚገኙ ተሟጋቾች ለክላይሜት ለውጡና ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂዎች ያደጉ ሀገሮች በመሆናቸው - ለመፍትሔው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው ይላሉ፡፡

በክሊኮ ምርምር አንፃር፣ ኢኮሎጂካል ኢንስቲቱት በተለያዩ ሀገሮች በመዘዋወር ፖሊሲ ኃላፊዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ አካሂዷል፡፡ የመስክ ምርምሩ ያተኮረው በሰብአዊ ደኅንነትና በአዳፕቴሽን ዙሪያ ሲሆን፣ የሁለትዮሽና ብዙዎች እርዳታ በታዳጊ ሀገሮች ዘንድ ለአዳፕቴሽኑ ያለውን አስተዋጽኦንም ተመልክቷል፡፡ ለምሳሌ፡- የፍልስጥኤምን ‹‹ክላይሜት ለውጥ አዳፕቴሽን ስትራቴጂን መርሀ-ግብር›› በመቀመር የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (ዩ ኤን ዲ ፒ) ወሳኝ ሚና ተጫውቷል፡፡ ነገር ግን የለጋሾች ሚና ለአዳፕቴሽን ጥረት የራሱ ችግር አለው፡፡ ከክሊኮ ምርምር ሁለት ትምህርት መቅሰም የቻላል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የለጋሾች እርዳታ ጠቃሚ መሆኑ ባያጠራጥርም በሀገራቱ ውስጥ ያሉትን ግጭቶች ይበልጥ አወሳስቧቸዋል፡፡ በሥልጣን ላይ ያሉ ኃይሎች አዳፕቴሽኑን በመተግበር ወቅት የራሳቸውን ጥቅም ያራምዳሉ፡፡ ሁሌም ዕውነት ባይሆንም አዳፕቴሽኑ ያተኮረባቸው ወገኖች የለጋሾች እርዳታ አሉታዊ ውጤት አለው የሚል አመለካከት አላቸው፡፡ አዳፕቴሽንን በተመለከተ የሚካሄደው ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ ፖለቲካዊ ውዝግብ እንዳለው መገንዘብ ያሻል፡፡

በምሥራቅ ኢትዮጵያ የሚገኙ የሱማሌ ፓስቶራሊስቶችን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል፡፡ እዚያ ለነፃነት የሚታገሉ ወገኖች አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች መንግሥት የሚረዳውን የሰፈራ እንቅስቃሴ የመንግሥትን ኃይል የሚያጠናክርና የኅብረተሰቡን መተዳደሪያ የሚያዳክም ነው ብለው ይሟገታሉ፡፡ በሌላ በኩል የፓስቶራሊዝም አኗኗር ካሁኑ የሕዝብ ብዛት ጋር የማይጣጣም መሆኑ የታወቀ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መገንዘብ የተቻለው ኢንተርናሽናል ድጋፍ ሁኔታን በተመለከተ ነው፡፡ ኢንተርናሽናል ለጋሾች ሁሌም ቃላቸውን አይጠብቁም፡፡ የእርዳታ መጠንና ትኩረት በፍጥነት ይለዋወጣሉ፡፡ ያላደጉ ሀገሮች - ከኮፐንሀገን ውሳኔ በኋላ ቃል የተገባላቸውን እርዳታ ታሳቢ በማድረግ ያቀዷቸው አቅም ግንባታዎች፣ ተቋሞችና የሥራ መርሀ-ግብሮች ቆመው ቀርተዋል፡፡ ጊዜና ገንዘብ ወጥቶባቸዋል፡፡ የለጋሾች እርዳታ ግን አልተገኘም፡፡ ከዓለም አቀፍ ለጋሾች ይገኛል የተባለው የአዳፕቴሽን እርዳታ ጉዳይ ተአማኒነት አጥቷል፡፡ የአዳፕቴሽን እርዳታ በግልጽነት ላይ የተመሰረተ በዘላቂ መዕቀፍ ላይ ያረፈና የሚመለከታቸው ተጠቃሚዎችም የሚተማመኑበት መሆን አለበት፡፡

Translation by Yacob Arsano